# ለአየር ባየር ፖለቲካ ፊታውራሪዎች

**(Ethio-Eriteria Conference organizers)**

በኢትዮጵያ ሕዝብ እሮሮ ነጋዴዎች

በኢትዮጵያውያን ትግል ቀዝቃዛ ውሃ ከላሾች

በኤርትራውያን ሰቆቃ ቆማሪዎች

የኤርትራውያንን ብሶት ሸፋኞች

ሻቢያን ከወያኔ ለማዋሐድ መንገድ ጠራጊዎች

የባህዳን መልሕከተኞች።

ተነቃባችሁ አክ-እንትፍ ተባላችሁ

የአየር ባየር ፖለቲካ ይብቃችሁ ።

አገር ወዳድ መስላችው ምንደኞች

አዋቂ መስላችው ተኩላዎች

መሪ መስላችው ሴረኞች

ተቆርቃሪ መስላችው የባህዳን ቡችሎች

አስተዋይ መስላቸው ሆድ አደሮች

አስተባባሪ መስላችው ከፋፋዮች

የባህዳን ቱልቱላ ነፊዎች።

ተነቃባችሁ አክ-እንትፍ ተባላችሁ

የአየር ባየር ፖለቲካ ይብቃችሁ ።

ብትቀላቀሉ ይሻላችሃል ንስሐ ገበታችሁ

ላስትማራችው ምስኪኑ የዋህ ወገናችሁ

በእርዛት በረሃብ በጥማት በሚያልቀው ህዝባችሁ

ወያኔና ባህዳንን ተጋፍጦ ላቆየላችሁ።

እውነት ትወጣለች ትለመልማለች

ሐሰት ትደርቃለች ታጋልጣለች

ኢትዮጵያም በልጆቿ ትታዳገለች።

ከጎላ ምንጭ